# እግዚአብሔር ለአፍሪካ ያልው ፍቅር ረጅም ታሪክ

በጄሰን ሼን ድሮሺ

ትርጉም

መጋቢ ፍቅሬ ኃ/ማርያም ኖርቻ

መስከረም 2022 እ. ኤ. አ.

**እግዚአብሔር ለአፍሪካ ያልው ፍቅር ረጅም ታሪክ**

ጄሰን ሼን ድሮሺ

ከካምፓላ (የዩጋንዳ ዋና ከተማ) የመጣው ጄሰን ጥያቄ ለመጋቢ ጆን ማቅረብ በሚልው ክፍለ ጊዜ አፍሪካውያን ለምን ይህን ያህል መከራ እንደ ሚደርስባቸው አንድ ጠቃሚ ጥያቄ ለመጋቢ ጆን ጠየቀው። ጥያቄውም እንደ ሚከተልው አቅርቦት ነበር፤

> እግዚአብሔር ለአፍሪካውያን ይጠነቀቃል ወይ? እዚህ ጋ መግቦተ እግዚአቤሔር ረጅም ታሪክ አለው፤ ይሁን እንጂ በታሪክ ውስጥ እንደ አውሬ የተቆጥርን፣ በአሳዛኝና በአሳፋሪ ሁኔታ ለባርነት የተሸጥን የሰው ዘር ነን። ባለማቋረጥ በበሽታ፣በድርቅ እና በመከራ ናዳ የምንጎዳ ነን። ታዲያ እኛ በእግዚአብሔር ዘንድ ከሁሉ የተናቅን የሰው ዘር ነን ብለን መደምደም የለብንም ወይ? ብዙዎች ዩጋንዳውያን በየቀኑ ግልጽ በሆነ ሁኔታ በችግር ውስጥ ይኖራሉ። እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ እንደሚጠነቀቅ ተስፍ እንደሰጠ አውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ እንድገረም የሚያስገድደኝ ነገር ቢኖር ግን ለምንድር ነው እግዚአብሔር በተለይም አፍሪካን በጣም የሚጠላው?

እነዚ ቃላቶች ባነበብኩ ጊዜ ልቤ በሃዘን ተመታ፡፡ እስከ አሁንም ድረስ ሃዘን ይሰማኛል። ምናልባት ለመጀመሪያ ጊዜ ስለሰማኋቸው (እና የመጋቢ ጆን በመግቦተ እግዚአብሔር ጥበብ ላይ ያነሳቸው አራት ነጥቦች) ደግሞ ስመለከት፤ የእግዚአብሔርን ልብ በሚመለከት ለሁሉም ሕዝቦች ማለት አፍሪካዎያንንም ጨምሮ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን በቀጥታና በግልጽ በማንሳት ድምጽ ለመሆን ጓጉቻለሁ።

እኔ በማደጎ ከአፍሪካ ያመጣኋቸው የሦስት ልጆች አባት ነኝ። እንደዚሁም ደግሞ ለአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ስልጠና ለመስጥት፣ ወላጅ አልባ ሕጻናትንና ጧሪ የሌላቸው መበለቶችን ለመንከባከብ የአገልግሎት ቡድን አዘውትሬ ወደ አፍሪካ ይገኔ እኼዳሉ። አፍሪካን እወዳለሁ፣ እና ከቅርብ አመታት ወዲህ አፍሪካ ባጠቃላይ፣ በተለይም ጥቁር አፍሪካውያን በእግዚአብሄር የማዳን ዕቅድ ውስጥ የተጫወቱትን ቁልፍ ሚና እየተረዳሁ መጥቼያሉ። ዩጋንዳ ስለ ጥቁር አፍሪካውያን ከሚገልጸው የመጻሐፍ ቅዱስ ምልከታ ጋር ስለሚዛመድ አብዛኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምልከታዬን በዚሁ ማዕቀፍ ላይ አጥብቤዋለሁ፣ ይሁን እንጂ አሁንም ለአፍሪካ በአጠቃላይ ሰፋ ያለ ትርጉም ይሰጣል ብዬ አምናሉ።

የራሴ የግንዛቤ ጉዞ የጀመረው የብሉይ ኪዳን ፕሮፌሰር (አስተማሪ) ከሆንኩ በኋላና በተለይም የትንቢተ ሶፈንያስን መጽሐፍ ማጥናት ስጀምር ነበር። ሶፎንያስ ምናልባትም የጥቁር ዝርያ ያለው የይሁዳ ነቢይ ሳይሆን አይቀርም። ማጥናት ጀመርኩ፤ የጥናት ጉዞዬም ደግሞ ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ይዞኝ ነጉዶዋል፣ ስለዚህ ይህ አጭር ዳሰሳ በካምፓላ የሚገኘው ጄሰንና ሌሎችም እግዚአብሔር ለአፍሪካ ያለውን ፍቅር እንዲገነዘቡ እና በአፍሪካም ሆነ በሌላው አለም በክርስቶስ ላሉት ሁሉ በእግዚአብሔር ጽኑ ፍቅር ተሰፋ እንዲያደርጉ እንደሚረዳቸው ተስፋ አደርጋለሁ።

**የእግዚአብሔር የተመረጥ ነብይ**

የትንቢተ ሶፎንያስ መጽሐፍ እንዲህ በማለት ይጀምራል፤ "በይሁዳ ንጉሥ በአሞጽ ልጅ በኢዮስያስ ዘመን ወደ ሕዝቅያስ ልጅ፣ወደ አማርያ ልጅ፣ ወደ ጎዶልያስ ልጅ፣ ወደ ኩሺ[1] ልጅ ወደ ሶፎንያስ የመጣ

---

[1] "Cushi" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል በአዲሱ መደበኛ ትርጉም "ኩሲ" ተብሎ የተተረጎመ ሲሆን በዚህ ጽሁፍ ደግሞ "ኩሺ" የሚለውን ጥቅም ላይ ውሎአል።

የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው"(ሶፎንያስ 1፡1)[2] "ሶፎንያስ" ማለት "ያህዌ (እግዚአብሔር) ሰወረው" ማለት ነው። የስሙ ትርጉም ወላጆቹ በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን ሕያው ዕምነት የሚገልጽ ሲሆን እንደዚሁም ደግሞ ከ669-642 ዓክልበ[3] በነበረው የንጉሥ ምናሴ የጨለማው ዘመን ጊዜ በእግዚአብሔር ጥበቃ ላይ የነበራቸውን ተስፋ ያሳያል (ለተጨማሪ መረጃ 2 ነገሥ 21 ይመልከቱ)።

ይህ ብቻ አይደለም፤ ሶፎንያስ ከንጉሥ ዳዊት የዘር ሐረግ የነበረ የይሁዳ ሰው ነበር። ቅድመ አያቱም ከ729-686 ዓክልበ ግድም የነገሠው ንጉሥ ሕዝቅያስ ነበር፤ እርሱም በይሁዳ ታሪክ ውስጥ ከ640-609 ዓክልበ በነገሠው ከንጉሥ ኢዮስያስ የተሀድሶ ሥራ ብቻ ሊነጻጸር የሚችል ግዙፍ የመንፈሳዊ ተሀድሶ እንቅስቃሴ የመራ ንጉሥ ነው፣ ለተሀድሶ እንቅስቃሴው ደግሞ በ622 ዓክልበ የነበረው የሶፎንያስ ስብከት በብዙ እንደ ጠቀመው ይገመታል። በተጨማሪም ልንገነዘበው የሚገባን ነገር ቢኖር የሶፎንያስ አባት ኩሺ መሆኑን ነው፤ እና ይህ እውነታ ደግሞ ሶፎንያስ ቅይጥ ዘር የነበርው ነብይ መሆኑን ያሳያል። ኩሽ በጥንታዊትዋ አፍሪካ ይኖር ነበር፤ እና የሶፎንያስ ሴት አያቱ (የጎዶልያስ ሚስት) ከአይሁድ የንጉሳዊ የዘር ሐረግ ጋር የተጋባች አፍሪካዊት ሳትሆን አትቀርም፤ ስለዚህ የልጅዋን የዘር ሐረግ ለማስጠበቅ ስሙ "ኩሻዊ" ወይም "የኔ ጥቁር" ብላ ጠርታዋለች። ሶፎንያስ ከቅይጥ ዘር የሆነ ነብይ መሆኑ ደግሞ ያህዌ (እግዚአብሔር) በአብርሃም በኩል ሁሉንም የሰው ዘሮች በሚመለከት የገባውን የማዳን ተስፋ ቃል መፈጸሙን የሚያበሥር ነው (ዘፍ 12፡3፤ 22፡18)።

የሶፎንያስ ከሁለት ዘር የመሆኑ ታሪካዊ ዳራ ማስረጃ የሚሆነን በተለይም ስለኩሽ ከቅጣትና ከተሐድሶ ጋር አያይዞ በማጉላት የተናገረውን በመመልከት ነው። በመጀመሪያ በሶፎንያስ 2፡12 ላይ የተጠቀሰው ኩሽ[4] አስቀድሞ የእግዚአብሔር ፍርድ የተቀበለ ብቸኛ የሆነ ጎረቤት ነው። ምንም እንኳን የመጽሐፍ ቅዱስ እንግሊዝኛ ትርጓሜዎች ጥቅሱ ወደፊት የሚፈጸም አድርገው ቢገልጹትም፣ከታሪካዊ ዳራውና በዕብራይስጥ ቋንቋ ከተጻፈው እንደ ምንረዳው ከሆነ የኩሽ የፍርድ ጥፋት ቀድሞውንም ያለፈ መሆኑን ነው። በተለይም፣ ያህዌ "እናንተም ኩሽአውያን ሆይ በሰይፌ ትገደላላችሁ" ሲል በ663 ዓክልበ ኮሻውያን ይቆጣጠሩት የነበረውን የ 25ኛውን የግብጽ ሥርወ መንግሥት መውድቅ እና ነብዩ ናሆም ስለ ነነዌ ቀደም ብሎ ሲጽፍ "አንቺ በአባይ ወንዝ አጠገብ ካለችው በውሃ ከተከበበችው ከቴቢስ[5] ትበልጫለሽን" (ናሆም 3፡8) ብሎ የጠቀሰው ሊሆን ይችላል። ናሆም እንደተናገረውም ሶፎንያንስም ደግሞ ይህንኑ በመድገም፤ የጌታ ቅጣት የጀመረው በኩሽ እንደነበረና የኩሽ አወዳደቅ ምሳሌ ደግሞ የነነዌንም ውድቀት በቅርብ እንደ ሚመጣ ማረጋገጫ እንደሆነ ያሳያል (ሶፎንያስ 2፡ 13–15)።

---

[2] በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተካተቱት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት በተለየሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው።

[3] ዓመተ ከክርስቶስ ልደት በፊት።

[4] ደራሲው እንደ ሚያስረዱት ከሆነ፣ በጥንት ዘመን "ኢትዮጵያ" ተብሎ የሚታወቀው ሀገር የአሁን ዘመናዊ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን መላውን ጥቁር አፍሪካዎያንን የሚወክል መጠሪያ ነበር፤ በተጨማሪም በዕብራይስጥ "ኢትዮጵያ" የሚለውን שׁוּכ (ኩሽ) በሚለው ቃል ነው የተገለጸው ሆኖም በግሪኩ አብዛኛው በአፍሪካ የሚኖሩ ሕዝቦችን በመወከሉ ምክንያት "ኢትዮጵያ" የሚለውን ነው ጥቅም ላይ የዋለው።

[5] የአማርኛ አዲሱ መደበኛ ትርጉም "ኖእ አሞን" የሚለውን ተጠቅሟል።

ነገር ግን ሌላም ተጨማሪ ነገር አለ፣ ሶፎንያስ ኩሽን ለመላው አለም የሚሆን  የመጨረሻው ዘመን ብቸኛ የተስፋ ምሳሌ አድርጎ ገልጾታል። እግዚአብሔር ክፋትን ሁሉ በማስወገድ ፍትህአዊ ሥርዓትንና ሰላምን ስለሚያሰፍንበት ስለሚመጣው የጌታ ቀን ሲናገር ነብዩ እንዲህ ሲል ጽፎአል።

> በዚያን ጊዜ ሰዎች ሁሉ የእግዚሔርን ስም እንዲጠሩ፣ ተስማምተው እንዲያገለግሉት፣ አንደበታቸውን አጠራለሁ።ከኩሽ[6] ወንዞች ማዶ፣የሚያመልኩኝ፣የተበተኑት ሕዝቤ ቁርባን ያመጡልኛል (ሶፎንያስ 3፡9–10)።

ነብዩ እዚህ ላይ ወደፊት በተለይም አዲስ ኪዳን ሲፈጸም ሊሆን ያለውን አርቆ ያየው ራዕይ እጅግ አስደናቂና የሚያስደምም ነገር ነው። እስቲ ይህንን ነገር በዝርዝር ከመመልከታችን በፊት ወደ ኦሪት ዘፍጥረት የመጀመሪያዎቹ ማዕራፎች ድረስ የሚዘልቀውን የኩሽ ማነነት ለመዳሰስ እንሞክር።

**አፍሪካ በብሉይ ኪዳን ታሪክ**

የአፍሪካ ኩሻውያን ግዛት ማዕከል ያደረገው አሁን ያለውን የዘመናዊው የሱዳን አካባቢ አንስቶ በተጨማሪም ወደ ደቡብና ወደ ምስራቅ አቅጣጫ  በመስፋፋት በተለይም ደቡብ ሱዳንን፣ኢትዮጵያ፣ ኤርትራ፣ጅቡቲንና የሶማሊያ ክልሎች እንደዚሁም ቀይባሕርንም ተሻግሮ ጥንታዊትዋንም የሳባ ግዛት ሁሉ የሚያካትት ነበር።

ነቢዩ ሙሴም ከነዚህ አካባቢ የመጣች ሴት ሚስት አድርጎ አግብቶአል (ዘኁልቅ 12፡1)፣ በኋላም ከነዚህ ከአንዱ አካባቢ የመጣች ንግሥት በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን የንጉሥ ሰሎሞንን ዝና ሰምታ የንጉሡን ብልጽግናና ጥበብ ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም መጥታለች (1 ነገሥት 10፡1–10)። ከአንድ ሺህ አመታት በኋላም ኢየሱስ በአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች ልበ ደንዳናነት በተገረመ ጊዜ እንዲህ ሲል ተናግሮ ነበር፤ "በፍርድ ዕለት የደቡብ ንግሥት ከዚህ ትውልድ ጋር ተነስታ ትፈርድበታለች የሰለሞንን ጥበብ ለማየት ከምድር ዳርቻ መጥታለችና። እነሆ ከሰለሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ" (ማቴዎስ 12፡42)።

የኩሽ ግዛትን በተመለከተ ደግሞ በመጀመሪያ የምንማረው ከኤደን ከሚፈሱት ከአራቱ ወንዞች የአንዱ መዳረሻ እንደሆነ ነው (ዘፍጥረት 2፡13)። ይህ ግጥምጥሞሽ ደግሞ እግዚአብሔር ሕይወትን ወደ አፍሪካ ለማምጣት ያለውን ሀሳብ አጉልቶ ያሳያል። የኩሽ አካባቢና ከእርሱም ጋር የተቆራኙ ሰዎች በኖኅ የልጅ ልጅ በካም ስም ተሰይመዋል።

የሶፎንያስ ትንቢት ደግሞ ለግንዛቤያችን አስፍላጊ የሚሆነው፤ የኩሽ ልጅ ናምሩድ የጥንትዋን ባቢሎን የገነባ (ዘፍጥረት 10፡ 6–10 ) ሲሆን፣ በዚያም እግዚአብሔር የራሳቸውን ስም ከፍ ከፍ ለማድረግ የፈለጉትን ለማየት የወረደበትና ቋንቋቸውንም በመደባለቅ በምድር ሁሉ እንዲበተኑ ያደረገበት ሥፍራ ነው፣ (ዘፍጥረት 11፡1–9 ይመልከቱ)። ከኩሽ ዘር የሆኑት ደግሞ ወደ አፍሪካ አህጉር በተለይም በሰሜናዊ ምስራቅ ክፍል ወደሚገኘው የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ተበተኑ። እነዚህም ደግሞ እግዚአብሔር ሊባርካቸው ተስፍ ከገባላቸው "ቤተሰቦችና" "ሕዝቦች" መካከል አንደኛው ወገን ናቸው፣ በመጨረሻም በአብርሃም መሲሀዊ ዘር በኩል መርገምንና ጠላትን ድል በመንሳት በረከትን ወደ አለም  የሚያመጡ ናቸው።

---

[6] "ኩሽ" የሚለው ቃል በሁሉም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች "ኢትዮጵያ" ተብሎ ተተርጉሞአል። በሌላ አንጻር ደግሞ ደራሲው "ኢትዮጵያ" በሚለው ምትክ በጽሁፋአቸው በተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ትቅሶች በሙሉ "ኩሽ" የሚለውን ተከተው ተጠቅመዋል።

ለእባቡ የተነገረው፡-     በአንተና በሴቲቱ፣በዘርህና በዘርዋ መካከል፣ጠላትነትን አደርጋለሁ፤እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤አንተም ተርከዙን ተቀጠቅጣለህ (ዘፍጥረት 3፡15)።

ለአብርሐም የተባለው፡- የሚባርኩህን እባርካልሁ፤ የሚረግሙህን እረግማለሁ፤ በምድር የሚኖሩ ሕዝቦች፣ በአንተ አማካይነት ይባረካሉ (ዘፍጥረት 12፡3)።

ለአብርሐም የተባለው፡- ዘሮችህም የጠላቶቻቸውን ደጆች ይወርሳሉ፣ቃሌን ስለሰማህ የምድር ሕዝቦች ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ (ዘፍጥረት 22፡17–18)።

እንግዲህ ለዚህም ነው ጳውሎስ እንዲህ ሲል የጻፈው “መጽሐፍ፣ እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንደ ሚያጸድቅ አስቀድሞ በማየት ፣ ‘አሕዛብ ሁሉ በአንተ ይባረካሉ’ በማለት ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ አስታወቀው” (ገላትያ 3፡8)።

እሥራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ከተመለሱና የእሥራኤል መንግሥትም ለሁለት ከተከፈለ በኋላ ከሶፈንያስ አገልግሎት ቀደም ብሎ በነበሩ ጊዜያት፤ይሁዳ ከኩሽ ሕዝቦች ጋር ብዙ ፖለቲካዊ ስምምነቶች አድርጎ ነበር (ኢሳይያስ 1–2 ፤ 20፡5–6)። እንደዚሁም ደግሞ የኢየሩሳሌም መንግሥታዊ አመራር ከአፍሪካውያን ጋር ጠንካራ ወዳጅነት መስርቶ ነበር (2 ሳሙኤል 18፡21፤ ኤርምያስ 38፡7፤ 39፡16)። ይህም ደግሞ የሶፎንያስ ሴት አያቱ ኩሻዊት እንደነበረች የበለጠ ያስረዳል።

**አፍሪካ በሌሎች ትንቢቶች**

ነብዩ ኤርምያስ እንዲህ ሲል ይጠይቃል፣ በውኑ “ኢትዮጵያዊ [በጥሬው፣ ኩሻዊ የሚለውን ይወክላል] መልኩን፣ ነብር ዝንጉርጉርነቱን መለወጥ ይችላልን?”(ኤርሚያስ 13፡23)። በተደጋጋሚ እንደ ምንመለከተው ኩሻውያን የቅጣት እና ደግሞም የተሀድሶ ትንቢታዊ መለዕክቶች አካል ናቸው። ቅጣትን በሚመለከት እግዚአብሔር ግብፅንና ኩሽን ድል ለማድረግ አሶርን እንዴት እንደ ሚጠቀም ግልፅ አድርጎአል፣ ይህም የምንረዳው በዚህ ምክንያት በይሁዳ ላሉት እንዲህ ይላል “በኩሽ ተስፋ ያደረጉ፣በግብፅ የተመኩ ይፈራሉ፤ ይዋረዳሉም።” (ኢሳይያስ 20፡5)፤ በተመሳሳይ ሁኔታ ደግሞ ከሶፎንያስ ቃል በሚስማማ መልኩ ሕዝቅኤል እንዲህ ሲል ያውጃል “ ቀኑ ቅርብ ነው፤የእግዚአብሔር ቀን ቅርብ ነው፤” ይልና ደግሞ በመቀጠልም “በግብፅ ላይ ሰይፍ ይሆናል፤ በኩሽም ላይ ጭንቀት ይመጣል” (ሕዝቃኤል 30፡ 3–4)።

ነገር ግን ልክ ኢሳይያስ የመሲሁ መንግሥት እንደ ሚመጣና አለሙን ሁሉ እንደ ሚያዳርስ እንዳበሰረው፤ እግዚአብሔር በሚሰራበት በመሲሁ ዘመን ደግሞ የኩሽ ቅሬታ የግዚአብሔር ታላቅ አዲስ ዘፃአት አንዱ አካል ይሆናል።

> በዚያም ቀን ጌታ እጁን ዘርግቶ እንደገና የተረፈውን የሕዝቡን ቅሬታ ከአሦር፣ከታችኛው ግብፅ፣ ከላይኛው ግብፅ፣ ከኩሽ፣ ከኤላም፣ ከባቢሎን፣ ከሐማትና ከባሕር ጠረፍ ምድር ይሰበስባል። ለመንግሥታት ምልክትን ያቆማል፤ ከእሥራኤልም የተሰደዱትን መልሶ ያመጣቸዋል፤ የተበተኑትን የይሁዳ ሕዝብ፣ ከአራቱ የምድር ማእዘን ይሰበስባል (ኢሳይያስ 11፡11–12)።

እንደዚሁም መዝሙረኛው በተመሳሳይ ጉጉት የእግዚአብሔር አዲስ ልደት ምስክር ወረቀት ከሚሰጣቸው መካከል አፍሪካውያን ቅሬታዎች እንደሚገኙበት ተናግሮ ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር በቤተሰቡ መካከል ሙሉ ልጆች አድርጎ ይቆጥራቸዋል፣ የምትታደሰውም ኢየሩሳሌም አዲሱ ቤታቸው ትሆናለች።

> “ከሚያውቁኝ መካከል፣ራዓብንና ባቢሎን እጠቅሳለሁ፤እነሆ ፍልስጤምንና ጢሮስ ከኩሽ ጋር፣ ይህ ሰው በዚያ ነው የተወለደው ይላሉ።” በእርግጥ ስለ ጽዮን፣ “ይህም ያም ሰው በእርሷ ውስጥ ተወለዱ፤ልዑልም ራሱ ያጸናታል” ይባላል። እግዚአብሔር ሕዝቡን ሲመዘግብ፣ “ ይህ ሰው የተወለደው በዚያ ነው” ብሎ ይጽፋል (መዝሙር 87፡ 4–6)።

## ከኩሽ ወንዞች ማዶ

እስቲ አሁን ወደ ሶፎንያስ ምዕራፍ 3 ተመልሰን እንመልከት። እዚህ ላይ እግዚአብሔር ከይሁዳና ከዚያም ባሻገር ያሉትን ታማኝ ቅሬታዎች እርሱ እስከ ሚፈርድበት ቀን ድረስ “ይጠብቁኝ” ሲል ያሳስባል (ሶፎንያስ 3፡ 8ሀ)። እንዲህ ያለውን ትዕግሥት የሚጠይቅ እምነት ለማበረታት ሁለት ምክንያቶችን ደግሞ ያስቀምጣል፡- (1) አሁንም የምድርን ነገዶች (አሕዛብን) እና ሃይላትን (መንግሥታትን) ሰብስቦ ሊቀጣቸው እንደ ወሰነ ይናገራል (ሶፎንያስ 3፡8ለ) እና (2) ከእነዚህ ሕዝቦችም መካከል ከብዙ ብሔር ብሔረሰቦች የተወጣጡ ቅሬታዎች እርሱን ለዘለዓለም እንዲያመልኩት በማደስና በማጽናት አጠራለሁ ይላል (ሶፎንያስ 3፡9–10)።

ክፍሉ እንዲህ ይነበባል፣

> “በዚያን ጊዜ ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ስም እንዲጠሩ፣ተስማምተው እንዲያገለግሉት፣ አንደበታቸውን አጠራለሁ። ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ፣ የሚያመልኩኝ፣ የተበተኑ ሕዝቤ ቁርባኔን ያመጡልኛል (ሶፎንያስ 3፡9–10)።

“የኩሽ ወንዞች” ምናልባትም ነጭ አባይና ጥቁር አባይ የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም (ኢሳይያስ 18፡1–2 ይመልከቱ)። በመቅደሱ ውስጥ እግዚአብሔር ለመማለድ መስዋዕት ይዘው የሚጓዙትን ማየት በአንድ ወቅት የምርኮኞች ልጆች የነበሩትንና አሁን ግን ከኤደን እየፈለሱ ከታላቁ ንጉሥ ጋር ሕብረት በማድረግ ለመደሰት የሕይወት ምንጭ የሆኑትን ወንዞች እየተከተሉ እንደሚሄዱ ይመስላሉ (ዘፍጥረት 2፡10–14 ከራዕይ 22፡1–2 ጋር በማነጻጸር ይመልከቱ)። እና እነዚህ አምላኪዎች ከዓለም ሕዝብ ሁሉ የተወጣጡ “ሰዎች” እና ከብዙ ብሔር ብሔረሰቦች የተሰበሰቡ ሲሆን በተለወጠ የንግግር ዘይቤ የእግዚአብሔርን ስም የሚጠሩ ናቸው።

እዚህ ጋ ሶፎንያስ የተመለከተው ነገር ቢኖር በባቢሎን ግንብ ወቅት የቋንቋ መደበላለቅ የነበረውን የተገላቢጦሹን ይመስላል። በ (ዘፍጥረት 10፡8–10) እንደ ተጻፈው ኩሻውያን ባቢሎንን እንደገነቡ እናስታውሳልን።እነዛ ግንቡን ሲገነቡ የነበሩት የራሳቸውን “ስም” ለማስጥራት ፈልገው ነበር (ዘፍጥረት 11፡ 4)። “እግዚአብሔር በዚያ የመላውን ዓለም ቋንቋ ስለ ደባለቀ የከተማይቱ ስም [ቦታው] ባቤል ተባለ። ከዚያም እግዚአብሔር ሰዎቹን በምድር ሁሉ በተናቸው” (ዘፍጥረት 11፡9)። በዚያም እግዚአብሔር “ቋንቋን” ደባለቀ የሚለው የዕብራይስጡ ቃል በሶፎንያስ 3፡9 ላይ “አንደበታቸውን አጠራለሁ” ተብሎ ከተተረጎመው ጋር ተመሳሳይ ነው፤ እንደዚሁም ደግሞ “በምድር ሁሉ በተናቸው” ለሚለው በሶፎንያስ 3፡ 10 “የተበተኑትን ሕዝቤ” የሚለውን ተመሳሳይ ቃል ይጠቀማል። የሚገርመው ግን በመጽሕፍ ቅዱስ ውስጥ ባጠቃላይ ስለ “ስም”፣ ስለ“ቋንቋ” እና “መበታትን” የሚለውን ግስ አንስቶ የሚናገረው በዘፍጥረት 11 እና በሶፎንያስ 3 ላይ ብቻ ነው።

እግዚአብሔር በኩሽ ላይ ቅጣትን እንዳወጀ በሰፎንያስ 2፡12 ላይ እንመለከታለን። አሁን ደግሞ በሶፎንያስ 3፡9–10 ባለው ላይ በአንድ ወቅት እግዚአብሒር ቁጣውን አፍስሶባቸው የነበሩ በሩቅ ምድር ላሉ እንኳን እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ቅሬታዎች በእግዚአብሒር ሕልውና ወደ ታድሰችው ኢየሩሳሌም እንዲመጡ

ያስገድዳቸዋል፤ ይህም የባቤልን እርግማን ይቀለብሳል። ነብዩ የኩሽ አካባቢን እንደ የእግዚአብሔር የመጨረሻ ዘመን የአዲስ ፍጥረት የተሀድሶ ብቸኛ ምሳሌ እንደሆነ ከፍ አድርጎ አቅርቦታል።

ታዲያ ከዚህ ትንቢት ጋር በተያያዘ አዲስ ኪዳንስ የሚናግረው እንዴት ነው?

## የአንድ አፍሪካዊ ድነት

ወንጌላዊ ሉቃስ የሐዋሪያት *ሥራ* መጽሐፍን በሚጽፍበት ወቅት ሶፎንያስ 3፡9–10 ሊያስታውስ እንደሚችል እርግጠኛ የምሆን ይመስለኛል። በሐዋርያት *ሥራ* 1፡8 እንደተጻፈው "እስከ ምድር ዳር ድረስ" ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ የማደረጉን ተልዕኮ አውድ ከማብራራት አንጻር ጴጥሮስ በጴንጤቆስጤ ቀን ስብከቱ  በሐዋርያት *ሥራ* 2፡17–21 ላይ ከትንቢተ ኢዩኤል 2፡28–32 ላይ ሲጠቅስ እንመለከታልን፤ ይህም የጌታን ቀን ከማሳየቱም በተጨማሪ በሶፎንያስ 3፡8–9 የእግአብሔርን ስም ከመጥራት ጋር አመሳስሎ ጠቅሶታል። በኢዩኤል ያልተጠቀሰ ነገር ግን በሶፎንያስ 3፡9–10 ባለው ላይ የተለወጠ ወይንም "የታደሰ አንደበት" በሴፕቱጀንት (ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ በተተረጎመው ጥንታዊ መጽሐፍ ቅዱስ) ደግሞ " ቋንቋ" የሚለውን ተጠቅሞአል፤ ይህም ደግሞ በአንድነት የማምለክ ራዕይ ማሳያ ሲሆን፤ ሉቃስ ደግሞ ሁለቱንም በማጣመር የ"ቋንቋዎች" መፍሰስ እና የጥንቶቹ አማኞች የነበራቸውን አስደናቂ ሕብረት በሐዋርያት *ሥራ* 2፡4፣ 11 እና በሐዋሪያት *ሥራ* 2፡42–47 በዝርዝር ገልጾታል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ግሪካውያኑ የጥንቶቹ ኩሻውያንን "ኢትዮጵያ" ብለው ጠርተዋቸዋል፤ በሌላ አንጻር ደግሞ ሉቃስ እንደ ሚነግረን ከሆነ "ከሰማይ በታች ካለው ሕዝብ" መካከል ከመጡት ውስጥ በሚገርም ሁኔታ ኢትዮጵያ የሚለው ስም ዝርዝር ውስጥ ሳይካተት ቀርቶአል (የሐዋርያት *ሥራ* 2፡5፣ እንደዚሁም (ከቁጥር 9–11 ደግሞ ይመልከቱ) ። ምናልባት "ኢትዮጵያ" ፈጽሞ ያልጠቀሰበት ምክንያት ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በመጥቀስ የሶፎንያስን ራዕይ ለማጉላት ስለፈለገ ሊሆን ይችላል፤ (የሐዋርያት *ሥራ* 8፡26–40 ከኢሳይያስ 56፡3–8 በማመሳከር ይመልከቱ)። ልንገነዘበው የሚገባ ነገር ቢኖር፣በመጀምሪያ ወደ ክርስትና የተለወጠ ከአሕዛብ ወገን የሆነ ቢኖር ኩሻዊ መሆኑን ነው፤ ይህ ደግሞ እግዚአበሔር በሶፎንያስ እንደተናገረው ከበዙ ሕዝቦችና ብሔር ብሔረሰቦች የተወጣጡ የአምልኮ ማህበረሰብ ቅርጽ የማስያዝ ራዕይ መፈጸም መጀመሩን ጎላ አድርጎ ያሳያል።

## ተስፍ ለሁሉም ሰዎችና ሕዝቦች

ሶፎንያስ ሊመጣ ባለው ነገር ላይ የተናገረበት ሁለተኛው መንገድ ደግሞ በአዲስ ኪዳን በኢየሱስ ትንሳኤ "ሕዝቦችን ሁሉ ደቀመዝሙር" የማድረግ አለማቀፍ እንቅስቃሴ መቀስቀሱን ነው (ማቴዎስ 28፡19)። በዚሁ መሰረት የኢየሱስ ተከታዮች የጌታን ታላቅነት ምስክርነታቸውን በመስጠት "በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ" ተንቀሳቅሰዋል (የሐዋርያት *ሥራ* 1፡8)።

በሶፎንያስ 3፡9–10 በተነገረው መሠርት፣ የሶፎንያስ የተሀድሶ ተስፋ ሰፋ ባለሁኔታ መፈጸሙን ስንመለከት፤ የኢየሱስ የመጀመሪያ ምጽአት የመጀመሪያውን የፍጥረት ዘመን  መገባደጃ መጀመሩን ሲያመለክት ደግሞ ከአዲሱ ኪዳን ጋር የሚጣጣም የአዲስ ፍጥረት ጅማሬ ዘመን መምጣቱን ደግሞ ያበሥራል (2 ቆሮንጦስ 5፡17፤ ገላትያ 6፡15፤ ዕብራውያን 8፡ 13 ይመልከቱ )። በመሆኑም በዚህ ዘመን በክርስቶስ ያሉትን ሁሉ የአብርሃም ዘር፣ በኢየሱስ በኩል የእግዚአብሔር ልጆች የተደረጉና የተስፋው ቃል ደግሞ ወራሾች አድርጎ ይቆጥራቸዋል (ገላትያ 3፡8፣ 16፣ 29፤ 4፡4–6)። አሁን አንድ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው ያልው፤ እርሷዋም ቤተክርስቲያን ናት (ኤፌሶን 2፡14–16)። ይህ ማለት ደግሞ ኩሻውያን የሁኑ እነ ስምኦን/ኔጌር አይሁዳውያን የሆኑ እነ ሳኡል/ጳውሎስን የመሳሰሉት ሁሉ በአንድነት በአንጾኪያ በነበረችው አጥቢያ

ቤተክርስቲያን ማህበረምዕመናን አካል ሊሆኑ ችለዋል (የሐዋርያት ሥራ 13፡1)፤ ደግሞም እንደነ ቲቶ ያሉ ከግሪክ ወገን የነበሩ ክርስቲአይኖች መገረዝ አላስፈለጋቸውም ነበር (ገላትያ 2፡3)።

ኢየሱስ ክርስቶስ "ከነገድ ሁሉ፣ ከቋንቋ ሁሉ፣ ከወገን ሁሉ፣ ከሕዝብ ሁሉ" ሰዎችን በመዋጀት "የካህናት መንግሥት" እንዲሆኑ በመሥራት ላይ እንዳል ራዕይ 5፡9–10 ይነግረናል፤ እንደዚሁም ራዕይ 7፡9–10 ይመልከቱ። በሐዋሪያት ሥራ 8፡26–40 ላይ ባለው ክፍል ጌታ ኢየሱስ በአፍሪካዊው ፖለቲከኛ መዳን የፍጻሜውን ጅማሬ ቀስቅሶአል፤ ይህም ደግሞ - ከዘፍጥረት እስከ ሶፎንያስ እንደዚሁም እስከ  ራዕይ አላማውን ለመፈጸም በድንቅ ለሚሰራው ለእግዚአብሔር አለማቀፍ ውዳሴ የሚያመጣ ይሆናል። በሶፎንያስ 3፡9–10፣ ሶፎንያስ ወደፊት ሊሆን ያለውን እንደ ተመለከተው አሁን እኛ  ከብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ያለን ክርስቲያን ካህናት ለእግዚአብሔር የምስጋና መስዋዕት (ሮሜ 12፡1፤ ዕብራውያን 13፡15–16፤ 1 ጴጥሮስ 2፡5) "በጽዮን ተራራ እና . . . በሰማያዊትዋ ኢየሩሳሌም" እያቀረብን ነው (ዕብራውያን 12፡ 22፤ ኢሳይያስ 2፡2–3፤ ዘካርያስ 8፡ 20–23; ገላትያ 4፡26)።

ይህ ሁሉ በእንዲህ እንዳለ፣ "አዲሲቷ ኢየሩሳሌም" እንደ አዲስ ምድር ከሰማይ የምትወርድበትን ቀን በመጠባበቅ ላይ እንገኛልን (ራዕይ 21፡2፣10፤ ኢሳይያስ 65፡17–18 በማነጻጸር ይመልከቱ)። ከዚያም መርገም ከቶ በሌለበት ሥፍራ ለመሆን፣ በክርቶስ የበላይነትና ብቃት ረፍትን ፍለጋ የምናደርገው የየዕልት ጉዞዋችን ፍጻሜ ይሆናል ((ማቴዎስ 11፡28–29፤ዮሐንስ 6፡35 ፤ራዕይ 21 22–22:5)። በዚያም ቀን፣ በክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሁሉንም የእግዚአብሔር ልጆች፡- ጥቁሮችና ነጮች፣ አይሁዶችና አሕዛብ፡- በእርግጥም የእግዚአብሔርን ስም በአንድነት ይጣራሉ፣ በመጨረሻም ነጻ በመውጣታቸው ይደሰታሉ።

**በእርግጥ እግዚአብሔር አፍሪካን ይወዳል ወይ?**

ስለዚህ እግዚአብሔር ለአፍሪካዎያን ያስባል ወይ? መጽሐፍ ቅዱስ እና ታሪክ ይህንን በአዎንታ ያስረግጣሉ። ከመጀመሪያው እግዚአብሔር ሆነ ብሎ የሕይወትን ውኃ ወደ አፍሪካ በመምራት የተጠሙትን ላማርካት እና ምድረ በዳውንም ለም ለማድረግ ያለውን ዓላማ ገልጿል (ዘፍጥረት 2፡13)። የዓለም ታሪክ እንደ ሚያስረግጠው ደግሞ ጌታ የአፍሪካዎያን ኃጢያት እንደ ሌሎችም ሕዝቦች ኃጢአት ጠበቅ አድርጎ ይመለከተዋል፣ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አፍሪካውያንን በማዳን እና መታደሳቸውንም በመጠቀም በቀሪዎቹ ሥራዎቹ በዓለሙ ሁሉ ሊሳራ ላሰበው ነገር የተስፋ ምልክት አድርጎ ደግሞ ስለሚያያቸው የተደሰተ መሆኑን ይመሰክራል።

በሐዋርያት ሥራ 8፡26–39 ኢትዮጵያዊውን ጃንድረባ በማዳን ጌታ በባቢሎን ግንብ የነበረውን አደናቃፊውን የጥፍት ውጤት መቀልብስ መጀመሩን በማብሰር (ዘፍጥረት 11፡1–9 ከ ሶፎንያስ 3፡9–10 በማነጻጸር ይመልከቱ)፤ በዘመኑ ፍጻሜ ለኢየሱስ ሁሉንም አቀፍ በሆነ ውዳሴ የሚደመደመውን አለማቀፋዊውን  ጉባኤ አስታዋውቆአል (ራዕይ 5፡9–10፤ 7:9–10)። የሕይወት ውኃው አሁንም ወደ አፍሪካ እየፈሰሰ ነው፣ የኢየሱስም የግብዣ ጥሪዎች አሁንም በመደወል ላይ ናቸው፡- "ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ" (ዮሐንስ 7፡37፤ እንደዚሁም ዮሐንስ 4፡10፣ 14 ይመልከቱ)። ጥሪውን ሰምቶ የሚመልስ ሁሉ "ዳግመኛ አይጠማም" ምክንያቱም እርሱ "ወደ ሕይወት ውሃ ምንጭም ይመራቸዋል፣እግዚአብሔር እንባን ሁሉ ከዐይናቸው ያብሳል" (ራዕይ 7፡16–17)። በአፍሪካ እና ከዚያም ባሻገር ላሉቱ ሁሉ እንዲህ ዓይነቱ  ተስፋ ተገበቶላቸዋል።

*ጀሰን ድሮሺ በሚድ ዌስተርን ቲዎሎጂካል ሰሚናሪ የብሉይ ኪዳንና የመጽሐፍ ቅዱስ ነገር መለኮት የምርምር ፕሮፌሰር በመሆን እና እንደዚሁም በሃንድስ ቱ ዘፐሎው ሚኒስትሪስ (ዩኤሳኤ) (Hands to the Plow Ministries (USA).) የይዘት ገንቢና አለምአቀፍ አሰልጣኝ በመሆን በማገልገል ላይ ይገኛሉ። እሳቸውና ባለቤታቸው ከኢትዮጵያ በማደጎ  ሦስት ልጆች  የወሰዱ ሲሆን በሀገሬቱ ውስጥም አዘውትረው የቤት ክርስቲያን መሪዎችን በማሳልጥንና ድሆችን ደግሞ በመከባከብ ላይ ይተጋሉ። የሳቸው የመረጃ ድህረ ገጽ የሚገኘው <u>www.jasonderouchie.com</u> ላይ ነው። ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ በመጋቢ ፍቅሬ ኃ/ማሪያም ኖርቻ የተተረጎመ ሲሆን በመጀመሪያ በ DesiringGod.org, April 7, 2022፡ <u>https://www.desiringgod.org/articles/the-long-history-of-gods-love-for-africa</u> በጀሰን ሼን ድሮሺ ስም በእንግሊዝኛ  “The Long History of God’s Love for Africa,” በሚል ታትሞአል።*